የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 27 እና 28

1. ይሁዳ ለሊቀ ካህናት የመለሰውን ብር ምን አደረጉት?
ሀ) ከመባዕ አስገቡት
ለ) ለስደተኛ መቀበርያ የሚሆን ቦታ ገዙበት
ሐ) እንደ ንስሐ ተቀበሉት
መ) ሁሉም

2. "የእስራኤል ልጆች የተሰማሙበትን የከቡርን ዋጋ ሠላሳውን ብር ወሰዱ፤ እግዚአብሔር እንደ አዘዘኝም ለሸክላ ሠሪ እርሻ ሰጡት " ብሎ ትንቢት የተናገረው ማን ነበር?
ሀ) ኢሳይያስ ለ) ኤርምያስ ሐ) አሞጽ መ) ዘካርያስ

3. ለእስራኤል በፋሲካ እስረኞች የሚፈቱበት ምክንያት ምንድን ነበር?
ሀ) ወንጀለኞች ቢሆኑም ባይቀጡ ይሻላል ተብሎ
ለ) ወንጀለኞች ከማኅበረሰቡ እንዳይራራቁ እና ብቸኝነት እንዳይሰማቸው
ሐ) ከግብጽ የወጡበት በዓል እንደመሆኑ ሕዝቡ ከእስር፣ ከግብጽ የወጡበትን ስለሚያከብሩ
መ) ሁሉም

4. የጲላጦስ ሚስት ማን ትባላለች?
ሀ) ማርያም ቀልዮጳ ለ) አብሮቅላ ሐ) ቤርሳቤህ መ) ቬሮኒካ

5. ጲላጦስ ሚስቱ "ያን ደግ ሰው እንዳትበድል አስተውል " ብላ መልእክት ከላከችበት በኋላ ምን አደረገ?
ሀ) እርሷን ሰምቶ ጌታ እንዳይሰቀል ወሰነ
ለ) በአደባባይ እጁን ታጥቦ አሳልፎ ሰጣቸው
ሐ) ራርተው ይተዉታል ብሎ አሳልፎ ሰጣቸው
መ) ለ እና ሐ

6. "ልብሶቼን ለራሳቸው ተካፈሉ፤ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ " ብሎ ትንቢት የተናገረው ማነው?
ሀ) ኢሳይያስ ለ) ንጉሥ ዳዊት ሐ) ኤርምያስ መ) ዘካርያስ

7. ከጌታ ሞት በኋላ ከተፈጸሙት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ) 500 የሚሆኑ ጻድቃን ከሞት ተነስተው በኢየሩሳሌም ተመላለሱ
ለ) መርገመ ሥጋ ጠፋ
ሐ) የቤተመቅደስ መጋረጃ ተቀደደ
መ) ኢየሩሳሌም ፈረሰች

8. በጌታ ስቅለት ጊዜ የሚሆነውን ሁሉ በሩቅ ሲመለከቱ ከነበሩት ሴቶች ውስጥ ያልነበረችው ማን ናት?
ሀ) ማርያም ባውፍልያ
ለ) መግደላዊት ማርያም
ሐ) የቀልዮጳ ሚስት ማርያም
መ) መልሱ የለም

9. ጲላጦስ ስለ ጌታ ሥጋ መሰረቅ የጭፍሮቹን የሐሰት ምስክርነት ከሰማ በኋላ ምን አደረገ?
ሀ) የተለያየ ምስክርነት ስለሰጡ ውሸት መሆኑን አውቆ በሰይፍ አስፈጃቸው
ለ) በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ፣ መስክሮ፣ በኋላም ሰማዕትነትን ተቀብሏል
ሐ) ያሉትን አምኖ ሐዋርያትን ሊቀጣ ፈለገ
መ) ሀ እና ለ

10. ጌታ ከተነሳ በኋላ ለዘጠ ሐዋርያት በየት ተገለጠ?
ሀ) በገሊላ ለ) በጌቴሴማኒ ሐ) በቀራንዮ መ) በጎልጎታ

11. "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ " የሚለው ቃል በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ስፍራ ይገኛል?
ሀ) ማቴ 1፡1 ለ) ማቴ 27:46 ሐ) መዝ 21፡1 መ) ለ እና ሐ

12. "ቤተመቅደስን የምታፈርሰው በሦስተኛውም ቀን የምትሰራው አንተ ሆይ" ይህንን የተናገሩት እነማን ናቸው?
ሀ)የሰቀሉት ጭፍሮች ለ)ጲላጦስ እና ሔሮድስ ሐ)በዚያ ያልፉ የነበሩት መ)የአስቆሮቱ ይሁዳ

13. የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል እንዲሸከም አይሁድ ያስገደዱት ማንን ነው?
ሀ) ቀሬናዊ ስምዖን ለ) ዮሴፍ ዘአርማትያ ሐ) የቀኙን ወንበዴ መ) የግራውን ወንበዴ

14. በዚህ ጻድቅ ሰው ላይ እንዳትበድል እወቅ ብላ የመሰከረችው ማን ናት?
ሀ)ከአገልጋዮቹ አንዷ ለ) የጲላጦስ ሚስት ሐ)የሔሮድስ ሚስት መ) የአልዓዛር እህት ማርታ

15. የጲላጦስ ጭፍሮች ከመዘባበታቸው በፊት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን አላደረጉም?
ሀ)ዘንግ አስያዙት ለ)ቀይ ልብስ አለበሱት ሐ)የእሾህ አክሊል ጎነጎኑበት መ) ነጭ ልብስን አለበሱት

16. አይሁድ በበዓል ልማዳቸው መሠረት እንዲፈታላቸው የጠየቁት ማንን ነበር?
ሀ)ኢየሱስ ክርስቶስን ለ)ኒቆዲሞስን ሐ)ዮሴፍን መ)በርባንን

17. ጲላጦስ በማቴ ምዕራፍ 27 ያደነቀው ምንድን ነው?
ሀ) የካህናት አለቆችን ክስ ለ)የኢየሱስ ክርስቶስን ዝምታ ሐ) የሕዝቡ ሽማግሌዎች ድምፅ መ) ሁሉም

18. የካህናት አለቆች ብሩን ወደ መባ ያልጨመሩት እና የደም መሬት የገዙበት ለምንድን ነው?
ሀ) የደም ዋጋ ስላለበት
ለ) መሬት ላይ ስለተበተነ
ሐ) ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲይዙ የከፈሉት ስለሆነ
መ)ሀ እና ሐ

19. አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ መጨረሻው ምን ሆነ?
ሀ) በብሩ መደሰት ለ) አብሮ መሰቀል ሐ) ታንቆ መሞት መ) መቅበዝበዝ

20. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሙስ ማታ በሊቀ ካህናት ግቢ ታስሮ ካሳለፉ በሓላ አርብ ጠዋት ወዴት ተወሰደ?
ሀ) ወደ ሔሮድስ ለ)ወደ ጲላጦስ ሐ)ወደ ሐና ግቢ መ) ወደ ጎልጎታ